PANORAMA # XXIV

የትዝብት አድማስ

ግንቦት 8 2000 ዓም

<u>ወያኔና የሱዳን መሪዎች</u>

የኢትዮጵያና የሱዳን ሕዝቦች በተፈጥሮ አጋጣሚ ምክንያት ጎረቤቶች በመሆናቸው ፥ ለዘመናት በሰላምና በወንድማማችነት በጉርብትና የኖሩ ለመሆናቸው ማስረጃ ይምጣለት የሚባል ጉዳይ አይደለም። መንግሥቶቻቸው በሚፈጥሩባቸው ጭቀናና በደል ምክንያት አንዳቸው ወደ ሌላው ሀገሮቻቸው በመሰደድ በጥገኝነት የቆዩባቸውን የተለያዩ ወቅቶች ዘርዝሮ ሊጨርሳቸው የሚችል አይኖርም። በሰው ሰራሹ የፖለቲካ ችግርም ይሁን በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት የሱዳን ሕዝብ ወደ ኢትዮጵያ እየተሰደደ ችግሩን እንደሚያሳልፍ ሁሉ፥ እኛም ወደ ሱዳን እየተሰደድን የመከራውን ጊዜ ስናሳልፍ ቆይተናል። ፋሽስቷ ኢጣሊያ በ1928 ዓም በወረረችን ወቅት ወደ ሱዳን ተሰድደው የመከራውን ዘመን ያሳለፉት ኢትዮጵያውያን/ት ለዚህ ሀቅ ታሪካዊ ምስክር ይሆናሉ። ወደ ሱዳን ዘልቆ በመግባት ለተዋጊ አርበኞቻችን የጦር መሳሪያ ሲያሸጋግሩ ከነበሩት አርበኞች መካከል ፥ ይልማ ሽበሽ ( በኋላ ጀኔራል) ገሪማ ታፈረ፥ አየለ አባ ጓዴ/ጓንዴና ሌሎቹም ሊጠቀሱ የሚችሉ ነበሩ። አሁንም በበርካታ ሽዎች የምንቆጠር ኢትዮጵያውያን/ት በምድረ ሱዳን በተለያዩ ከተማዎች በስደት እንገኛለን። የደርግንና የወያኔን ጭፍጨፋዎች በማምለጥ ለበርካታ ዘመናት የቆዩባት ምድር ሱዳን ነች።የሱዳን ሕዝብም የወንድማማችነት ፍቅሩንና ትብብሩን አልነፈገንም። ለዚህም እኮ ነው ከበርካታ ዓመታት በፊት የታወቀው የሲዳን ድምፃዊ ተጨዋች <u>መሀመድ ወርዲ</u> የሚከተለውን ዘፈን ያንጎራጎረው። " ኢትዮጵያ ወ ሱዳን አክዋን አክዋን" ኢትዮጵያና ሱዳን ወንድሞማቾች ናቸው ለማለት ነው። ይህንን ቁም ነገር የተመላበትን ጣዕመ ዜማም፥ የእኛው ተዋቂ አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ በዐረብኛ ቋንቋ በመዝፈኑ ምክንያት የሱዳን ሕዝብ ደስታውን እንደገለፀለት የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያስታውሰው መልካም ትዝታ ነበር። ዛሬ ነገሩ፥ "ያማ ቀርቶ ሌላ ዘፈን መጥቶ" ሆኗል።

ሱዳን በ1960 ዎቹ ከእንግሊዝ ቅኝ ተገዥነት ነፃነቷን ስትቀናጅ የመጀመሪያው ጠቅላይ ሚንስተር ከነበረው ከእስማኤል ኤል አዝሃሪ ጀምሮ፥ የኢብራሂም አቡድ ፕሬዝደንትነትን ጨምሮ እስከ ጃአፋር ኤል ኑሜሪ አስተዳደር ድረስ የነበሩትን የሱዳን ዘመነ መንግሥታት መገንዘብ ከተቻለ፥ እንደ አሁኑ ያለ አይን ያወጣ የሱዳን ጥቃትና ወረራ፥ ድፍረት ንቀት በኢትዮትጵያ ላይ መከናወኑን አናስታውስም። ዛሬ ድንበራችን ተደፍሮ፥ መሬታችን ተወርሶ፥ ዜጎቻችን ታፍነው ተወስደው፥ ሀበት-ንብረታችን፥ ቤት አዝመራችን ተቃጥሎ፥

ደኖቻችን ተመንጥረው ዝናራችንም ተፈትቷል።ቀበቷችንንም አስወልቀውናል፡
፡ የወቅቱ የሱዳን መሪዎች! ይህም በመሆኑ፥ የዳግማዊ ቴዎድሮስና የራባኢይ
ዮሐንስ አፅሞች በመካነ መቃብሮቻቻው ውስጥ እየተገለባበጡ ይገኛሉ። ዛሬ፥
ዛፎቹ ተመንጥረው ቁጥቋጦቹ ዛፍ መሆናቸውን በመረዳታቸው፥ የወቅቱ
የሱዳን መሪዎች ጊዜ ጠብቀው የቆየ ኀልማቸውን ዕውን በማድረግ ላይ
ይገኛሉ። ይህ በወቅቱ እየተከናወነ ያለው ክስተት እንዲሁ በድንገት የመጣ፥
እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውሃ ፈሳሽ ግብታዊ ርምጃ አይደለም።
የቆየ-የደነደነ ዕቅድ የነበረው፥ አመች ጊዜ ሲጠብቅ የነበረና አድፍጦና ነቅቶ
በመጠባበቅ ቆይቶ፥ "ብረቱ ሲግል ለመቀጥቀጥ" የተዘጋጀ ነበር።
ኢትዮጵያን ለማጥቃትና ለመከፋፈል አመች ጊዜ ሆኖ ያገኙት አሁን መሆኑን
የተረዱት የሱዳንና የግብፅ መሪዎች፥ አጥብተው ያሳደጉትን የውስጥ
ወኪላቸውን ወያኔን እንደ ትሮጃን ፈረስ ወይም የውስጥ ቅጥረኛ በመጠቀም
ላይ ናቸው። የወያኔ መሪዎችም ወደ ሥልጣን ያበቋቸውን የበላይ ጠባቂዎቻቸ
ውን ውለታ ለመክፍልና በጫካ ሳሉ የተዋዋሉትን ግዴታ ለመወጣት
የሚያደርጉትን ርምጃ በማናለብኝ ማከናወናቸው ማንንም ሊያስገርም የሚችል
አይሆንም። በወያኔ መሪዎችና በሱዳን ባለሥልጣናት መካከል የስምምነት
ድርድር የተከናወነው፥ ወያኔዎቹ ጫካ በነበሩበት ጊዜ ለመሆኑ፥ይህንን በቅርብ
ሲከታተሉ የነበሩ ሀገር ወዳድ ታጋዮች በጊዜው ቢያስታውቁም ሰሚ አላገኙም
ነበር። ሁሉም ጆሮ ዳባ ልበስ እያለ በአርምሞ እየተመለከተ አሳለፈው። የደርግ
ባለሥልጣናትም ዓይናቸውን በመጨፈን ጊዜውን እየጠበቀ ሊፈነዳ የሚችል
የወያኔን የተቀበረ ቦምብ ለማየት ዓይነ ኅሊናቸው ሊመለከተው አልቻለም።
ይህ አልበቃ ብሏቸው ሀቀኛ የኢትዮጵያን የቁርጥ ቀን ልጆች በመጨፍጨፍ
ጊዚያቸውን አጠፉ። የሱዳን ባለሥልጣናትም፥በዕቅዳቸው መሠረት
ኢትዮጵያን የሚያጠፉላቸውን የውስጥ ድርጅት የሚያስፈልገውን ርዳታና
ትብብር በመለገስ፥ ኢትዮጵያን እንዲቆጣጠር አደረጉ። የወያኔ ጦር አዲስ
አበባ የገባው ከሱዳን መንግሥት በተሰጠው የጦር መሳሪያ ፥ታንክንም ጨምሮ
በመጠቀም መሆኑ የቅርብ ጊዜ አሳፋሪ ትዝታና ሰቆቃ ነው። ኢሕአፓን ከመ
ውጋትና ከጀርባም ከማጥቃት አንፃር ሱዳን የተጫወተው አስከፊ ሚና ገና
የተረሳ አይደለም።

የወያኔ መሪዎች ከባዕድ አለቆቻቸው በተሰጣቸው መመሪያና ዕቅድ መሠረት፥
ለአለፉት አስራ ሰባት ዓመታት በቅደም ተከተል የሚከተሉትን ኢትዮጵያን
የማጥፋት ተግባራት ሲያከናውኑ ቆይተዋል። ዛሬ የመጨረሻውን የዕቅዳቸውን
ምዕራፍ አመቻችተዋል።

1. በመጀመሪያ ያደረጉት፥ የኢትዮጵያን የመከላከያ ሠራዊትና ተቋማቱን
መበታተንና ማፈራረስ ነበር።

2. የኢትዮጵያን ሕዝብ በጎሳ፥በቋንቋና በሃይማኖት በመከፋፈል የአካባቢ
ንዑሳን የዘር አስተዳደሮች አዋቀሩ።

3. በወያኔ የፖለቲካ ፕሮግራም ላይ የተመሠረተ የጠባብ ብሄረተኛ ሕገ

መንግሥት በመፃፍ አንቀጽ 39ን አክለው ማንኛውም ክልል በተለይም የራሳቸው ክልል በአመቸው ጊዜ ከኢትዮጵያ  የሚገነጠልበትን ድልዳልና ማስፈንጠሪያ አዘጋጁ።

4. ከአጎራባች ክፍላተ ሀገራት፥ ከጎንደር፥ ከወሎና ከአፋር ለምና ሀብታም መሬቶችን ወደ ትግራይ በማጠቃለል ግዛታቸውን አስፋፉ። ይህንን ድርጊት የተቃወሙትን የጎንደርን የወሎንና የአፋርን ነዋሪዎች ገደሉ አሰሩ፥ አሳደዱ። በተለየም ታሪክ አዋቂዎችን፥ አዛውንቱንና መስካሪዎችን ሆን ብለው አጠፏቸው። ለዚህ እኩይ ተግባራቸወም ልዩ ትኩረት የሰጡት፥ በጎንደር ክፍለ ሀገር ነዋሪዎች ላይ ነበር።

5. በኢትዮጵያ  የጠረፍ  አካባቢዎች የማያቋርጥና መጠነ ሰፊ የሆነ ጦርነት  በመጀመር፥ ዕልቂትና ፍጅት በማካሄድ ላይ ናቸው። ይህ ደግሞ ያለ ምክንያት ሳይሆን፥ ለዕቅዳቸው የመጨረሻውን ምዕራፍ መዝጊያ የሚያስችላቸውን ሂደት ለማድረግ የታሰበ  ነው። ዛሬ በኦጋዴን  የሚካሄደው ጦርነት ከጠቅላላው የወያኔ ኢትዮጵያን የማፈራረስ ዓላማ ጋር ተያይዞ መታየት ይገባዋል።

6.  የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅምና ሀገራዊ አንድነት የሚያስጠብቅ ማዕከላዊ ኃይል ( ጠንካራና ብሔራዊ መንግሥት) አሳጥቶ በአንፃሩ ግን ሀገሪቱን ልክ ከቅድመ ቴዎድሮስ  በዘመነ መሳፍንት ስር እንደነበረቸው ኢትዮጵያ በማድረግ ፥ ሁሉም በየክልሉ ጎልውና ላይ ብቻ እንዲያተኩር አድርገውታል። ይህም ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ዜጎቿም እንደ ሕዝብ እንዳይቆዩ ለማድረግ ከታቀደው ጥፋት ጋር አብሮ የሚሄድ ነው። ለአለፉት አስራ ሰባት ዓመታት ይህን ዕቅድ በሥራ ለማዋል ልምምድ ሲደረግ ቆይቷል። “ብልጎ ከሞኝ በራፍ ሞፈር ይቆርጣል”  እንዲሉ፥ ወያኔ ለአለፉት አስራ ሰባት ዓመታት ይህንን ሲያደርግ ቆይቷል።

7. ዛሬ በኢትዮጵያ ሰሜን ምዕራቡ ክፍል የተከሰተው የሱዳን ወረራና ዝርፊያ ወያኔዎች ከሱዳን መሪዎች ጋር ያቀዱትና የተባበሩበት የወደፊቷን አዲሷን የትግራይን ሪፑብሊክ ለመመስረት የነበራቸውን ጎልም ተግባራዊ እንዲሆን የሚደረግ ሸርጉድ ነው። በሁለቱ ሀገሮች መካከል ወደፊት ስለሚኖረው ሰፊ የጋራ ድንበር ለማረጋገጥና ሊኖራቸው የሚችለውንም የወደፊቱ ዝምድና ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ ነው።  ታዲያ፥ የምዕራብ ኢትዮጵያን ሰፊ መሬቶች ሱዳኖች ሲወስዱት ዝም ብሎ ማየት ብቻ ሳይሆን የወያኔ መተባበር፥ ምን ትርጉም ሊሰጠው ይችላል?  ሱዳንና የወደፊቷ የወያኔ የትግራይ ሪፑብሊክ ስለሚኖራቸው የልማት፥ የንግድና የኢኮኖሚ ትብብር  አስፈላጊ የሆኑት መሠረተ ልማቶች የመተግበር ጅማሮዎች እየተከሰቱ በመሄድ ላይ ናቸው።  ከጣና የኢሊክትሪክ ኃይል መስመር በጭልጋ አቋርጦ፥ በመተማ አድርጎ ወደ ሱዳን የሚተላለፍ መስመር ተዘርግቷል ወይም በሂደት ላይ ነው። ከሱዳን እስከ ሽሬ እንዳ ሥላሴ የሚደርስ የባቡር መስመር የመዘርጋቱ እቅድ ማንንም ሊያስደንቅ የሚገባው አይደለም። ታላቋን የትግራይን ሪፑብሊክ

ለማየት የሚያቋምጡት የወያኔ ቡድኖች፥ “ የአክሱም ሐውልት፥ ለአማራ፥ ለወላይታ፥ ለጉራጌና ለሌላው የኢትዮጵያ ክፍል ምኑ ነው?” እንዳሉት ሁሉ፥ አክሱም ለሱዳን ምኑ እንደሚሆን መግለፅና ማስረዳት ሊኖርባቸው ነው:: በተለይም ከአንድ መቶ ዓመታት በፊት የማህዲስቶችን ወረራ ለመመከት ሲል ልክ እንደ አንድ ተራ ተዋጊ ወታደር ሲዋጋ የወደቀውን የአራተኛ ዮሐንስን አንገት በመቆረጥ በኦምዱርማን ከተማ እያዞሩ የተሳለቁት ሱዳኖች ናቸው ለትግራይ ሕዝብ የሚቀርቡት ካልተባለ በስተቀር! የወገኖቹን የኢትዮጵያውያንን ሀገርና ታሪክ የካደ፥ ያዋረደ፥ የሸጠና የለወጠ ከሀዲ ብሉቅባሽ ቡድን፥ ኢትዮጵያን ለማፈራረስ የከፈተውን የአጋንንት በረት ለመዝጋት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተባብሮ እንደሚነሳ ማወቅ ነበረበት::

8. ግብፅና ሱዳን የዓባይን ወንዝ በሚመለከት ያላቸውን ስጋት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሊያረጋጋላቸው የሚችል ታማኝ ወኪል በማስፈለጉ ምክንያት፥ ወያኔ ተቆራርሳ በምትተርፈው የኢትዮጵያ አካባቢ አስተማማኝ ኃይል እንዲሆንላቸው ይፈልጋሉ::ይህ ግን የጎልም እንጀራ እንጅ የሚሆን አይደለም፡

እኛ አኩሪ ታሪካችንን ጠቅሰን፥በታሪካዊ ማስረጃ በተደገፈ ሰነድ ተመርኩዘን፥ ሀቁን እየተናገርን፥ ጠላትን እያጋለጥን ከሕዝባችን ጋር በመተባበር ትግላችንን ከመቀጠል ሌላ የበለጠ ምርጫና ደስታ አይኖረንም:: ስለሆነም፥ ዛሬ በዚህ በእኛው ትውልድ ዘመን እየተፈፀመ ያለውን ጥቃትና በደል፥ እንዲሁ እንደ ወቅቱ የፖለቲካ ክስተትና ውሽንፍር ብቻ ልንቆጥረው አንችልም:: በዘመናት የሱዳን ሀገር አስፋፊና ወራሪ ባለሥልጣኖች የሀገራችንን ለም መሬት ለመውሰድ ሞክረው ነበር:: ሙከራቸው ሁሉ፥ በየወቅቱ በነበሩ ሀገር ወዳድ የኢትዮጵያ ልጆች ከፍተኛ መሥዋዕት በመክፈል ሲከሽፍ ቆይቷል፥ :: የኢትዮጵያ ሀገራችንም ዳር ድንበር እንደተከበረና እንደተጠበቀ ቆይቷል:: ወደፊትም ይኖራል:: ኢሕአፓም ትጥቅ ትግል በአካባቢው ሲያካሂድ፥ ከጎንደርና ጎጃም ሕዝብ ጋር ሆኖ የሱዳንን የመስፋፋት ዕቅድ ሲያከሽፍና ሲያግድ መቆየቱ በሕዝብ የሚታወቅ ነው::

ወራሪውን የድርቡሽን ጦር ለመግጠም ወደ መተማ የወረዱት፥
“ ዓፄ ዮሐንስ አራተኛ በ1881 ዓም በዕለተ ቅዳሜ በመጋቢት 1 ቀን ከጧቱ ሦስት ሰዓት ላይ ጦርነቱ ተጀምሮ ወራሪውን የድርቡሽ ጦር እያባረሩ ገላበት ድረስ ካሳደዱት በኋላ ከጠላት ወገን በተተኮሰ ጥይት ተመትተው ወደቁ:: ድርቡሾቹም አንገታቸውን በመቁረጥ ወደ ኦምዱርማን ወሰዱት:: ከሦስት ቀናት በኋላም የንጉሠ ነገሥቱን የተቆረጠ ጭንቅላት በእንጨት ላይ ሰክተው፥ በግመል ጀርባ ላይ አድርገው ገበያ ለገበያ፥ መንደር ለመንደር እያዞሩ በማሳየት የሱዳን ሕዝብ እንዲደሰትበት አደረጉ:: ” ሲሉ አንድ ታሪክ ፀሀፊ አቅርበውት ነበር::

ዓፄ ዮሐንስ መሥዋዕት  የከፈሉባት ኢትዮጵያ በየጊዜው እየተነሱ ሊያጠፏት የመጡትን ጠላቶቿን ድል እየተጎናጸፈች በነጻነቷ ስትኖር፥ የድርቡሾች ሱዳን ግን ብዙም ሳትቆይ፥ አንግሎ ኢጅብሻን የሚል ስም ተሰጧት በእንግሊዝ ቅኝ በመሆን ለዘመናት ቆይታለች።

ለሰማዕቱ ዮሐንስ  ሁኔታ ያዘነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ የሚከተለውን የሀዘን እንጉርጉሮ በማሰማት እንባውን አፍስሶላቸዋል።

“ዓፄ ዮሐንስ ሞኝ ናቸው፥
እኛም ሁላችን ናቅናቸው፥
ንጉሥ ቢሏቸው በመኸሉ፥
ወሰን ጠባቂ ልሁን አሉ፥
በጎንደር መተኮስ፥ በደንቢያ መታረድ አዝኖ ዮሐንስ፥
ደሙን አፈሰሰው እንደ ክርስቶስ፥
እንዳያምረው ብሎ ድሃ ወዳጁን፥
መተማ አፈሰሰው ዮሐንስ ጠጁን፥
የጎንደር ሃይማኖት ቆማ ስታለቅስ፥
አንገቱን ሰጠላት ዳግማይ ዮሐንስ፥
እጅግ ደስ ይለኛል ያንተ ስም ሲነሣ፥
የቁና አፈር ንሩግ አንተ ነህ ወይ ካሣ! ”

እንግዲህ ይህንን  አኩሪ ታሪክ በመካድና በማዋረድ ነው ዛሬ የኢትዮጵያ ምድር በባዕድ ሲወረር፥ ዜጎች ታፍነው ሲሄዱ፥ ሀገር ሲቃጠል፥  ሰማዕቱ ዮሐንስ ከተፈጠረበት ቦታ የመጡ የወያኔ መሪዎች ከሱዳን መሪዎች ጋር በመተባበር የራሳቸውን የድርጅት አጀንዳ ለማስፈፀም የሚፍጨረጨሩት። ምንም ተባለ ምን፥ የኢትዮጵያ የውስጥና የውጭ  ጠላቶች  በተባበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ተሸንፈው ሀገራችን በነፃነቷ መኖሯን ትቀጥላለች። የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ክተት መክት ብሎ በመነሳት ፥በጠላቶቹ ላይ ድልን በመጎናጸፍ ታሪካዊ ገድል እንዲያስመዘገብ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን። ኢሕአፓም ከሕዝብ ጎን ሆኖ በመታገል ኢትዮጵያን ያስከብራል።